**ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
**የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር**
**አዲስ አበባ፣**

**ጉዳዩ፣ በሶማሊያ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ሰራዊትን ይመለከታል፣**

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿም ሆነ ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት በሠላምና በመቻቻል መርህ ላይ የተመሰረተና ለጋራ ጥቅም የቆመ መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ፤ በተለያዩ ታሪካዊ ምክንያቶች በተለያዩ የቅርብና የሩቅ የውጭ ወራሪዎች ተደጋጋሚ ጥቃት እየተሰነዘረባት ሀገራችን በከፍተኛ መስዋዕትነት ራስዋን ስትከላከል ኖራለች።

«የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት» በመባል የሚታወቀው አክራሪ ቡድን በሌሎች ውጫዊ ኃይሎች እየታገዘ በኢትዮጵያ ላይ የ«ጅሐድ» ጦርነት በማወጅ በሀገራችን ላይ ግልጽና ወቅታዊ አደጋ ፈጥሮ እንደነበርና ጉዳዩ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይትና ምክክር ተደርጎበት መንግሥት ማንኛውንም ዓይነት የሀገሪቱን ጥቅምና ሠላም የሚያስጠብቅ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ መወሰኑና ይህንንም የምክር ቤቱን ውሳኔ ፓርቲያችን ኢዴአፓ-መድህን ሙሉ ለሙሉ ደግፎ መቆሙ ይታወሳል።

ሠራዊታችን በመንግሥት ውሳኔ መሰረት በአገራችን ላይ ተጋርጦ የነበረውን ግልጽና ወቅታዊ አደጋ ለማክሸፍ ወደ ሶማሊያ እየገባ በነበረበት ጊዜም ሆነ ሞቃዲሾ ከገባ በኋላ ይህንን ግዳጁን በተወጣ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ከሶማሊያ ለቆ እንደሚወጣ በመንግሥት በኩል በተደጋጋሚ ሲገለጽ የነበረ ቢሆንም፤ በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች በሶማሊያ ለረዥም ጊዜ መቆየቱ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ ሰራዊታችን ከሶማሊያ በሚፈለገው ፍጥነት ለቆ ለመውጣት ባለመቻሉ በአሁኑ ወቅት የሰራዊታችን አባላት ከመጠን ያለፈ መስዋዕትነት ለመክፈል የተገደዱ ሲሆን፤ ከፍተኛ የሀገራችን ሀብትም እየባከነ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ በሶማሊያ ውስጥ በየጊዜው እየተከሰቱ ባሉ ወታደራዊ ግጭቶች ምክንያት፤ የሀገራችንና የሕዝቧ መልካም ስምና ክብር በተለያዩ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንና የሰብአዊ መብት ድርጅቶች አማካይነት እየጎደፈ መሆኑ እንደቀጠለ ነው።

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ሰራዊት በሶማሊያ ያለው ቆይታ እያሳሰበን በመምጣቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በግንቦት ወር 2000 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ላይ ጉዳዩን በጥያቄ አቅርበን እንደነበር ይታወሳል። ይኸውም ሰራዊታችን እስከመቼና ምን ዓይነት ቅድመ ሁኔታዎች እስከሚሟሉ ድረስ በሶማሊያ እንዲቆይ ታስቧል? ሀገራችን መክፈል የሚገባውን መስዋዕትነት ሁሉ በብቸኝነት ተሸክማ ያለገደብ የምትቆየውስ እስከመቼ

ነው? የአፍሪካ ህብረትና ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በሶማሊያ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት ተፈጥሮ ሰራዊታችን ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ቃል በገቡት መሰረት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ የሚችሉትስ እስከመቼ ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን አቅርበን እንደነበረና ለእነዚህም ጥያቄዎች በወቅቱ ክቡርነትዎ መልስ ሰጥተው እንደነበር ይታወሳል፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

በወቅቱ ለእነዚህ የኢዴአፓ-መድህን ጥያቄዎች በሰጡት መልስ - ኢትዮጵያ ወደ ሶማሊያ ሠራዊት ለማዝመት ያስገደዳትን ዓላማ ለጊዜው ሙሉ በሙሉ እንዳሳካች፣ ነገር ግን በዋናነት ለሶማሌ ሕዝብ ጥቅም ሲባል በሶማሊያ እየታዩ ያሉት በጐ ሁኔታዎች እስኪጠናከሩና የአፍሪካ ህብረት ሠላም አስከባሪ ኃይል በበቂ መጠን እስከሚገባ ድረስ ሠራዊታችን እንዲቆይ ብናደርግ ተገቢ እንደሆነ፣ አለም አቀፉ ህብረተሰቡ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት ካልቻለና የኢትዮጵያ ሠራዊት በሶማሊያ የሚኖረው ቆይታ አላስፈላጊ ወይንም በቂ ነው ተብሎ በታመነት በማንኛውም ጊዜ ግን ሠራዊታችን ለቆ ሊወጣ እንደሚችል፣ ይህም መልዕክት በማያሻማ ሁኔታ ለአለም አቀፍ ኮምኒቲው በመንግሥት በኩል እየተላለፈ እንደሆነ ገልፀው ነበር፡፡

ይህ መልስ በክቡርነትዎ ከተሰጠ ወዲህ ሦስት ወራት ያለፈ ቢሆንም በሶማሊያ ያለው ሁኔታ ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሰ ሲሆን አለም አቀፉ ህብረተሰብም ምንም አይነት ተጨባጭ እርምጃ ሲወስድ አልታየም፡፡ አሁንም በሶማሊያ እየታየ ያለውን ከፍተኛ ጫና በዋናነት ተሸክማ የምትገኘው አገራችን ኢትዮጵያ ናት፡፡

መንግሥት በሀገራችን ላይ ተጋርጦ የነበረውን ግልጽና ወቅታዊ አደጋ ለመቀልበስ ወታደራዊ ኃይል ወደ ሶማሊያ ማዝመቱም ሆነ እስከ አሁን ድረስ በሶማሊያ ውስጥ ቆይታ ማድረጉ፤ ከኢትዮጵያ፣ ከሶማሊያም ሆነ ከአፍሪካ ቀንድ አጠቃላይ ጥቅም አንጻር ተገቢና ትክክለኛ እርምጃ እንደሆነ ፓርቲያችን ኢዴአፓ-መድህን በጽኑ ያምናል፡፡ ነገር ግን በዚህ ከኢትዮጵያና ከሶማሊያ ግንኙነትም አልፎ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ እንደምታ ባለው የሶማሊያ ሁኔታ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ መከፈል የሚገባውን መስዋዕትነት ሁሉ በብቸኝነት ተሸክማ ያለገደብ ከዚህ በላይ መቀጠል አለባት ብሎ ፓርቲያችን አያምንም፡፡

ስለሆነም፤ መንግስትዎ ጉዳዩን እንደገና በማጤን የኢትዮጵያን፣ የሶማሊያንና የአካባቢውን ጥቅም ግምት ውስጥ ባስገባ የኃላፊነት ስሜት የኢትዮጵያ ሰራዊት በጥንቃቄና በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከሶማሊያ ለቆ ሊወጣ የሚችልበትን ቁርጥና ግልፅ ውሳኔ መወሰን ይገባዋል ብሎ ፓርቲያችን እንደሚያምን በአክብሮት ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ልደቱ አያሌው
ፕሬዝደንት

<u>እንዲታወቅ፣</u>

- ለመንግስትና ለግል መገናኛ ብዙሀን
  <u>አዲስ አበባ</u>